# ላያዛልቅ ጸሎት ለቅስፈት

ከአቶ ሰውየው

ዘንድሮ በአንጀኞች ሠፈር  ፍቅሬ ፍቅሬ ማለቱ በዝቷል። የኢሕአፓ አንጀኞች በፓልቶክ መድረካቸው ስለ አንድነት ትግል ሲያወሩ ከርመው የተለያዩ የድርጅት መሪዎችን እያመጡ ማነጋገር ከጀመሩ ከርመዋል። ቀደም ብለው ከኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ኅብረት አንድነት መሪዎች መካከል እነ አቶ ደረጀን በቅርቡ ደግሞ ከኦነጉ ሌንጮ ለታ፤ ቡርቱካን ሚደክሳን፤ ክፍሉ ታደሰን ባለፈው ሳምንት ደግሞ ኢንጂኔር ኃይሉ ሻውልን (ስለ እሳቸው ከዚህ መድረክ መገኘት ዝቅ ብዬ አስተያየት እሰጥበታለሁ) በዚህ ሳምንት ደግሞ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋን አስተናግደዋል። በአከታታይም እነ ገብሩ አሥራትን፤ ሥዩ አብርሃን እንዲያም ሲል እነበየነ ጴጥሮስንና መራራ ጉዲናንና ሌሎችንም እናመጣለን ቢሉን አይደንቀኝም። እኔስ የሚገርመኝ የፖለቲካ ድርጅት መሆናቸውን ረሱት ወይስ ወደ ሚዲያነት (የዜና ማሰራጫነት) ተቀይረዋል? ወይስ ይሄ ግርግር ሌላ የሚሰጠን መልዕክት አለ? ለህገራችን ተቃዋሚ የተሻለ የትግል ስልት ወይም አማራጭ ይዘው መጥተው ይሆን? በሌላ በኩል ደግሞ ከመድረካቸው የሚገኙትስ እነማንና ለምን ይሆን ለሚሉትና ለመሳሰሉት ጥያቄዎች ሰዎች የተለያየ መልስ ይኖራቸዋል።

የአንጀኞች አንዱ መሪ ለንድን ገብቶ ሀገር ቤት ልገባ ነኝ ይላል አሉ። ትግሉም ይኸው ኢትዮጵያም ያቻትና ግባና ታግለህ አሳየን ነው የእኔ መልስ። ብዙ አትገላግሉት። ትግሉ በሀገር ቤት መሆኑን የተረዳው በቅርቡ መሰለኝ። ወያኔ ሥልጣኑን ከያዘ ጀምሮ ዕምነታቸውን ሳይሸጡ በጽናት የሚታገሉና የሚያታግሉ ወገኖች በሀገር ቤት ከፍተኛ መስዋዕትነትን ከፍለው ታሪክን ሠርተው አልፈዋል። ምናልባትም ረስቶት ይሆናልና እነ ጋይምን እጠራለታለሁ።  አሁንም በየዕለቱ ምስዋዕትነትን እየከፈሉ ነው። ምናልባትም በሀገር ቤት ውስጥ የድርጅት ጽ/ቤት ያላቸውንና የነበራቸውን ቢጠይቅ ትግሉ ምን እንደሚመስል ሊያስገነዝቡልኛል። የሠለጠነ የሸወዳ ፖለቲካ የሚያስተምሩትም ካሉ ከሠፈሩበት ተራራ ወርደዋልና መጠየቅ ነው። ሌላኛው የአንጀኞች መሪ ተብዬ ደግሞ ሁለተኛ ቀይ ሽብር ይፋፋም ከሚባልበት የከረንት አፌርስ የፓልቶክ መድረክ ብቅ ብሎ ኦነግ ስለኢትዮጵያዊነቱ አይን አፋር ሆኖ ነው እንጂ አንድነትን ሊቀበል የሚችል ድርጅት ነው ብሎ ሊመሰክር ሲዳዳው ተሰምቷል። የኦነግን ድረ-ገጽ የተመለከተና የሚጽፉትን አንብቦ የሚረዳ ብዙ ወገን አለና የዚህን ፍጡር ምስክርነት የአይጥ ምስክር ድንቢጥ የሚለውን ያስታውሷል። ምናልባትም የኦነጉ ሌንጮ ለታ ከመድረኩ መጥቶ ኢሕአፓ ስለ ኦሮሞ ሕዝብ ምን ያገባዋል ያለውን አምኖበት ይሆናል። ኦነጎች ኢትዮጵያዊነታቸውን የሚያምኑ ከሆነ እነሱ ራሳቸው ያውጁ፤ ኢትዮጵያዊነታቸውን በግብር ያሳዩንና እናምናቸዋለን። እኔማ አንድ ወገኔ አንጀኞች ያቃጣሪነት ፖለቲካ ነው የተያያዙት ያለውን ያስታውሰኛል። እነሆ የኦነግ ድረ-ገጽ (http://www.oromoliberationfront.org/) የሚለውን ያንብቡ።

The Oromo Liberation Front (OLF) is a political organization established in 1973 by Oromo nationalists to lead the national liberation struggle of the Oromo people against the Abyssinian colonial rule. The emergence of the OLF was a culmination of a century old yearn of the Oromo people to have a strong and unified national organization to lead the struggle.

እንግዲህ አንጀኞች በኢሕአፓ ውስጥ ባሉበት ወቅት አንስተው በአብዛኛው የኢሕአፓ አባላት ውድቅ ተደረገባቸው ከሚባሉት ጥያቄዎች አንኳር አንኳሩን ብንመለከት ለምሳሌም ያክል "ወያኔን ወያኔ አትበሉት"፣"ኢሕአፓ ስሙን መቀየር አለበት"፣ "አፊዳፊት ፈርመን በመግባት ሕጋዊ እንሁንና" ከዓመት ተኩል በፊት ደግሞ በዶ/ር ጌታቸው ሲገፋ የነበረው በካናዳ ኦቶዋ ኮንፈረንስ ላይ የቀረበው "የ2010 ምርጫ ፖለቲካን አስመልክቶ ያቀረበውን ጽሁፍ" ለተመለከተ (በነገራችን ላይ ያንን ጽሑፍ በተመለከተ ዶ/ር ጌታቸው በአሲምባ መጥቶ ያደረገውን የሞቀ ውይይት በአሲምባ ዳት ኦርግ ላይ አርካይቭ ያድምጡ "http://www.Assimba.org") አንጃው ያቀደውን ከሥራ ለማዋል ለሽፋን ሽር ጉድ ሲል ነው የምናየው። የእኔ ሙግት አብዛኛው የኢሕአፓ አባላት ውድቅ ያደገሩትን አመለካከት በጊዜው አንጀኞች በድርጅታቸው ማንሳታቸው ትክክል አልነበረም ለማለት አይደለም። ይሄማ ጸረ-ዴሞክራሲያዊነት ነው የሚሆነው። ነገር ግን አሁንም የምጠይቃቸውና ለእኔ ጸረ-ዴሞክራሲነታቸውንና ጸረ-የሕግ የበላይነትን ያስመሰከሩበት ሁኔታ ላስቀምጥ። ሀሳባቸው በብዙሃኑ ተቀባይነት ሲያጣና ይህንንም ሊመለከት የተቀመጠውን ሕጋዊ የድርጅታቸውን የበላይ አመራር የሆነውን <u>ጊዜያዊ ጉባኤ</u> ረግጠው ወጥተው ሕገ-ወጥ በሆነ መንገድ የድርጅት ንብረት፣ ስምና ማሕተም ወስደው "እኛ ነን ኢሕአፓ ያውም ዴሞክራሲያዊ" ሲሉን ተቀብለን ዕውቅና መስጠት ማንም ይሁን ማን ትክክል አይደለም። በአቋቋሙትም መድረክ መገኘትም በእኔ ዕምነት በድርጅቶች ውስጥ የማያስፈልግ ግርግርና ሁከት ፈጣሪዎችና ሃሳዊ መሲሆችን አጓጉል ዕውቅና መስጠት፣ <u>ላያዛልቅ ጸሎት ለቅስፈት ነው ባይ</u> ነኝ።

ባዘጋጁት መድረክ መገኘት የማንም ድርጅት ሙሉ መብቱ ነው። ነገር ግን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሕገ-ወጥነትንና ጸረ-ዴሞክራሲያዊነትን እያበረታቱ እንደሆነ እንዲያዝልኝ እፈልጋለሁ። ከሁሉም በላይ የኢንጂኔር ኃይሉ ሻውል በዚህ መድረክ መገኘት እንዳሳዘነኝ የምገልጸው በሚቀጥለው ተረት ነው። <u>የፊት ጓደኛሽን በምን ቀበርሽው በሻሽ የዛሬው እንዳይሽሽ።</u> እስኪ እየተስተዋለ። ይህንን መልዕክቴን ያነበቡ የኢንጂኔር ኃይሉ ደጋፊዎች አስተያየታቸውን እንደሚለግሡኝ እርግጠኛ ነኝ።

ለማጠቃለል፦

- የአንጀኞች ውር ውርና አጓጉል የአዞ እምባ ዕውቅናን ለማግኘት የሚደረጉት የደካሞችና የልምጥምጦች ፈሊጥ እንጂ ለኢትዮጵያ ዴሞክራሲሪዊ ትግል አንዲት ቅንጣት መፍትሄ ሊያመጡ የሚችሉ አይደሉም። ከሁሉም በላይ ደግሞ ሕገ-ወጥ በሆነ መንገድ የያዙትን የኢሕአፓን ስምና ንብረት ይዘን እንቀጥላለን እስካሉ ድረስ መወገዝና መጠየቅ አለባቸው እንጂ ከነሱ መድረክ መሳተፍ ትልቅ ስህተት ነው።
- አጥፊ ኃይሎች ተሰባሰበው እውን ወያኔን እንኳን ቢተኩ የሕግ የበላይነትና፣ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ያመጣሉ ብሎ መጠበቅ በእኔ ዕምነት እብደት ነው። ሌቦች ቢተባበሩ እስኪ ዘርፉ እንጂ በክፍፍል ላይ መተራረዳቸው አይቀሬ ነው። በተለይም ከድርጅት በታኞችና ጠባብ ብሔረተኞች ዴሞክራሲና የሕግ የበላይነት ሊጠበቅ አይችልም። እኔ ኢትዮጵያዊ አይደለሁም የሚለኝን ሌንጮ ሊታን ዕመኑት አይናፍር ነው እንጂ በአንድነት ሊያምን ይችላል ብለው በአንፃሩ በኢትዮጵያዊነታቸው ላይ ያልተደራደሩ በፅናት ያታገሉ ወገኖችን እንደነ ኢያሱ ዓለማየሁና ድርጅታቸው ኢሕአፓ ላይ የውሸት ዘመቻ ማካሄድ የጤንነት አይደለምና ውሻ በበላበት የሚለውን ላስታውሳቸው እወዳለሁ።

- ድርጅቶችን ለማዳከምና ለመግደል የሚደረግን ማንኛውንም እንቅስቃሴ መቃወምና ማጋለጥ የእያንዳንዱ ሀገር ወዳድ ግዴታ ነው። በፍራቻና በይሉኝታ ከዳር ቆሞ እኔ ምናገባኝ የምተናነቀው ማለት ለኢትዮጵያዊነት መንኳሰስና ለትግሉ መሽመድመድ እኛም ከተጠያቂነት ነፃ ሊያደርገን አይችልምና ንቃቱ ያለን ወገኖች ዝምታውን እናቁም!

የማግለልን ፖለቲካን እንዋጋ፤ ዴሞክራሲያዊነት አይደለምና!
ለኢትዮጵያዊነት የታገለን ጽኑ ድርጅት ኢሕአፓን ለማግለል የሚደረግ ግርግር ሁሉ ውሎ አድሮ ይከሽፋል!

እምቢኝ ለዘረኞች! ለጠባቦችና ለበታኞች!
ኢትዮጵያዊነት በትግላችን ያለጥርጥር ያብባል!

አቶ ሰውየው ከሰሜን አሜሪካ
(ታኅሣሥ 5 ቀን 2001 — December 14, 2008)